# የመሪ መቀዬር ጊዜያዊ፣የሥርዓት ለውጥ መሠረታዊ!

እንደሚታወቀው ዶክተር አቢይ የኢሕአዴግ ጠቅላይ ሚኒስቴር ከመሆኑ በፊት፣ለብዙ ዓመታት ብዙ ወገኖቻችን የተገደሉበት፣የተጋዙበት፣የታሠሩበትና የተሰደዱበት እልህ አሥጨራሽ ትግል ያለማቋረጥ ተካሂዷል።

በተለይ ለ27ዓመታት ያለማቋረጥ በአማራው ላይ የሚደረገውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ ለማሥቆም  አማራው ባደረገው ያላሰለሰ ወደርየለሽ ትግል፣ ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ ደግሞ  የኦሮሞ ገበሬዎችን መፈናቀል በመቃወም የተነሳው የኦሮሞ ትግል፣የሌሎችም ብሔሮች ትግል፣ የዲያሥፖራውም ትግል ከHR128 ጭምር፣የነጩም ዓለም ከጎናችን የመቆም ጅማሮ ተደማምሮ፣ ትግሉ ተጠናክሮና ገፍቶ እያየለ በመምጣቱ፣ በዘር ሸንሽኖ እሥከዛሬዋ ዕለት ድረስ እያጋደለንና እያፈናቀለን የሚገኘውን፣ የትነግን|ኢሕአዴግን መንግሥት ወደመቃብሩ እያቃረበው እንደነበር ግልፅ ነው።

ሆኖም ግን ሥንት ነፍስ አልቆ፣ወደርየለሽ ግብግብ ሲደረግ ኖሮ፣ ትግሉ ጠንክሮ ነፍሰገዳዩ ትነግ|ኢሕአዴግ ሊወድቅ ሲንገዳገድ “ለሥር ነቀል ለውጥ ቆመናል፣ተቃዋሚ ነን” ይሉን የነበሩት የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የሕዝብን ዕምቢተኝነት ትግል በተወሰኑ ጣፋጭና ውብ ቃላት በመለወጥ ፣የሞተው ትነግ|ኢሕአዴግ በኦዴግ|ኢሕአዴግ ነፍስ እንዲዘራበት፣ ከማሥቻላቸውም በተጨማሪ  በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በወዶ ገባነት የነፍሰ ገዳዩ የኢሕአዴግ “የጥገና ለውጥ” ደጋፊዎች በመሆን እና ትግሉን  በማኮላሸት ሠቆቃችን እንዲራዘም አሥተዋፅዖ አድርገዋል።ይህ ይቅር የማይባል በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተሠራ ደባ ነው።

ዶክተር አቢይም የኢሕአዴግ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ በመምጣት፣ የአንድነትንና የኢትዮጵያዊነትን ካባ ለብሶ፣ህብረተሰቡ በቀላሉ የሚማረክባቸውን ጣፋጭ ቃላትና ላይ ላዩን የሚታዩ ነገሮችን ብቻ በመቅረፍ፣ ብዙውን ተቃዋሚና ማሰብ የተሳነውን የህብረተሰብ ክፍል  ከጫማው ሥር አሥገባው።

እሥኪ ዶክተር አቢይ ወደሥልጣን ከመጣ ወዲህ የተሠሩትና ሊሠሩ የታሰቡት ምንድናቸው?ጥልቀትስ አላቸው? ወይስ ለጊዜያዊ ፍጆታ ነው?ወይስ ሕዝቡን ለማዘናጋትና በሽንገላ ቃላት የነበረውን ሥርዓት ከትነግ|ኢ ሕአዴግ፣ በኦዴግ|ኢሕአዴግ በመተካት፣ ለማሥቀጠል?  እሥኪ እንዳሥሳቸው።

**ዛሬ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዶ|ር አቢይ የሚመራው የአራቱ የትህነግ፣የኦህዴድ(ኦዴፓ)፣ የድህዴን(ድዴፓ) እና የብአዴን(አዴፓ) የዘር ድርጅቶች ጥምረት ኢሕአዴግ  ከሌሎች የዘር ድርጅቶች ጋር በመሆን ፣አማራ ባልተካፈለበት በ1983ዓም የሽግግር ወቅት  የኢትዮጵያን አንድነት አጥፍቶ በዘጠኝ(9) የዘር ክልሎች በመተካት ዛሬ ያለውን ዘርን ከዘር የሚለያይና የሚያጋድል፣ከፋፋይ  ህገ መንግሥት ማፅደቁ ይታወሳል።**

ዶክተር አቢይ! <u>በዚህ ህገመንግሥት ሥር፣በእነዚህ የዘር ጥምር ድርጅቶች</u> መራጭነት ጠቅላይ ሚኒስቴር እንደሆነ ወዲያውኑ፣የዕርቅን፣ የእንደመርን፣ የሠላምን፣የፍቅርን፣ የኢትዮጵያዊነትንና የአንድነትን ጣፋጭ ቃላት ይዞ ብቅ አለ።

**በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብም፣**

(1) ለ27ዓመት ያልሰማቸው የኢትዮጵያን አንድነት ያካተቱ ቃላት "የኢሕአዴግ መሪ ነኝ" ከሚል ሰው በመሥማቱ፣በኢትዮጵያዊነቱና በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምነው አማራው፣ ደቡቡ ፣አፋሩ፣ጋምቤላው፣ቅልቅሉ፣የተወሰነው ኦሮሞ ወዘተ በተስፋ ደገፈው።

(2)ዱሮም ወንጀል ያልሰሩ መታሰር የማይገባቸው ንፁህን አማሮች ዛሬም ድረስ በትግሬ እሥር ቤቶች እንደሚሰቃዩና ጠያቂ እንዳጡ ቢታወቅም፣አዲስ አበባም ሆነ ሌሎች ቦታዎች የነበሩትንና የታወቁትን ኢትዮጵያውያኖች ከእሥር ማሥፈታቱንም በደስታ ተቀበለው።

(3) ጳጳሶቹን ማሥማማቱንም እንዲሁ፣ (4)ምን እንደተፈራረሙ ባይነገርም ፣በኤርትራና በኢትዮጵያ መካከል ግንኙነት ማደሱንም በጥሩ ጎኑ አየው።

(5) በአጠቃላይ በውጭም በውስጥም ያሉ ተቃዋሚ ኢትዮጵያውያን ለምርጫ እንዲዘጋጁ መናገሩንም፣በበጎ ጎኑ ተቀበለው።

(6) "የቀን ጅቦች፣ሌቦች ወዘተ" ብሎ አምርሮ መሄዱን፣እና

(7) ወንጀሉ ውስጥ አቢይ ይኑርበት አይኑርበት ለጊዜው የምናውቀው ነገር ባይኖርም "ሌቦችና ወንጀለኞች" የሚባሉትን መያዝ መጀመሩን፣ በመሳሰሉት ሙሉ ድጋፍ ተቸረው።

**ከዚህ በኋላስ አቢይ!**

(1)በተቃዋሚዎች በኩል <u>የሽግግር መንግሥት</u> እንዲቋቋም ሃሳብ ቢሠነዘርም፣የአቢይ መልስ "እኔ አሽጋግራችኋለሁ"ነው።

በዚህ ጊዜ ተቃዋሚው ዕውነተኛ ተቃዋሚ ቢሆን ኖሮ ጫና ፈጥሮ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ይታገል ነበር።አለበለዚያ የተጀመረውን ትግሉን ገፍቶ ለውጥ ያመጣል እንጅ ተበርካኪ አይሆንም ነበር።ይህ "እኔ አውቅላችኋለሁ" ተቀባይነት የለውም።ሁልጊዜ መሪ ብቅ ሲል ዓይንን ጭፍኖ የሚሠጥ ድጋፍና ሠማይ መሥቀል መጨረሻው አያምርም፣ ውድቀት ያሥከትላልና።

(2)አቢይ! ትግሬ ሄዶ"ትግሬዎች በእሳት የተፈተናችሁ ወርቆች ናችሁ" አለ።ቀጥሎም ኦሮሚያ ውስጥ የታሰሩት፣ በቅርቡ በነበረው ግጭት ቦንብና የኮንትሮባንድ ዕቃ የተገኘባቸው ትግሬዎች ናቸው።ሥለወንጀላቸው ሳይሆን <u>ለትግሬ ሕዝብ ክብር ሲባል</u> ማድረግ የሚገባንን እናደርጋለን ብለን ተወያይተናል"በማለት <u>ዓይን ያወጣ ሙሥናውን በገሀድ ተናገረ</u>።

(3)በመቀጠልም በዚሁ በትግሬው ሥብሰባው "እኔ እምመኘው ወልቃይትና አርማጨሆ አካባቢ ያሉ ዲያሥፖራዎች ወደአገራቸው መጥተው የሕዝቡን ኑሮና ችግር እንዲያዩት።

ሕዝቡ እያለ ያለው ት|ቤት፣ጤና ጣቢያ፣መንገድ፣መብራት፣ ከዚህ ውጭ ያለው አጀንዳ የሕዝብ አጀንዳ አለመሆኑን ሲያውቁ ፣ብዙዎቹ ሳያውቁ የሚደናገሩት ከሕዝብ ጋር ይሆናሉ" ብሎን አረፈው። እንዲህ ነው ጠ|ሚኒስቴር ማለት!

የወልቃይት ጥያቄ የማንነት ጥያቄ እንደሆነ እየታወቀ የትግሬ ወራሪዎች"እንኳን አማራውን ወረሩት" የሚል ቁልጭ ያለ ወገናዊነትን ያሥተናገደ መልዕክት አሥተላልፏል። ይህ በአማራው ህልውና ላይ ፈርዶ፣ለትግሬው ነፍሰገዳይ መወገኑን በግልፅ አሳይቷል።

(4)"ከእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ "እንዲሉ፣ይውጣላችሁ ብሎ ነው መሰለኝ፣እዚያው ትግሬ ውስጥ "አሁንም እኔ የማምነው ጎንደር ግማሽ አካሉ የእናንተ አካል ነው።ጎንደር አካባቢ ያለው ችግር የሚፈታው በጀመራችሁት መንገድ ብቻ መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ" በማለት ለትነግ ትግሬዎች ዕምነቱን አጠናክሮላቸዋል።

(5) ጎንደር ሄዶ ደግሞ ፣የሕዝቡን ሥሜት እንዴት ልቀስቅሰው፣በማለት ይመሥላል፣ሥለ እነአፄ ፋሲል፣ሥለ ጎንደር ገናናነት፣ወዘተ ባዶ ድሥኩር ደሥኩሮ እና ሕዝቡንም አሥጨብጭቦ ሞጋች ሳያገኝ ተመልሷል።

(6) ባህር ዳር ላይ፣(1) አቡነ አብርሀም! ከተጨባጩ ሁኔታ ተነሥተው "መናገር ቀላል ቢሆንም በተግባር ሊከብድ እንደሚችል" ሲነግሩት በፀጋ ከመቀበል ይልቅ፣ አቢይ ሲመልስ እንደመሪ ሳይሆን እንደተራ ካድሬ፣"ይህ ግልብ የሆነ አሥተሳሰብ ነው" በማለት ኃይለ ድምፅ በተላበሰ ተግሳፅ ደመደመ።

(2) አንድ የነቃ የአማራ ወጣት ደግሞ ሁለት ነገሮችን ሰነዘረ። አንደኛው "አማራው አሮሚያ ክልል ውስጥ የራስ ገዝ አሥተዳደር ያሥፈልገዋል"የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው "ለአማራውና ለኦሮሞው ደም መቃባት ምክንያት የሆነው የአኖሌ ሀውልት ነው" የሚል ነው። አቢይ ሲመልስ "በአማራውና በኦሮሞው መካከል እዚህ ባህር ዳር ላይ የተደረገውን መልካም ግንኙነት እንዲደፈርስ ነው ወይ የምትፈልጉት?" የሚል ማሥፈራሪያ መሠል መልስ ሠጠ። በአማራው ላይ ለሚያድርገው ቅጥ ያጣ ጫና "በቃህ" መባል አለበት።

(7)አዲስ አበባ ላይ ትግሬዎችን ብቻ ሰብስቦ."እኔ እያለሁ ምንም አይደርስባችሁም" ማለቱም አንዱ አነጋጋሪ ነገር ነበር።

(8) አቢይ! የአማራውን መደራጀት አሥመልክቶ አብን ብቅ ሲል፣"ያሥፈራል" በማለት ድብቅ ፀረ አማራነቱን አንጨባርቋል።

ከሁሉም የሚገርመው የገደለን፣የረገጠንና በዘር የከፋፈለን የኢሕአዴግ ሥርዓት ሳይፈርስ እንዲቀጥል ካላቸው አቋም አንፃር፣ትናንት ከተቋቋመ አንድ ለጋ ድርጅት "አብን"ጋር፣ የአዴፓና የኦዴፓ ባለሥልጣናት የሚያደርጉት ተቃውሞ ለበስ የአሻጥር ሩጫ ነው።

ይኸውም አሁን በቅርቡ አማራው በሁሉም አካባቢዎች ሠላማዊ ሠልፍ መቼ! እንደሚያደርግ ባለሥልጣኑ እያወቁ፣የሰላማዊ ሠልፉ ዕለት "ተሠርቶ ያላለቀ ፕሮጀክት ለመመረቅ" በሚል አቢይ ጭምር አማራ ክልል ሄዶ መረቀ።የዚህ ዋናው ምክንያቱ ደግሞ የአቢይ አጋር የሆነው የእነገዱ አዴፓ በአማራው በኩል ያለው ድጋፍ አነሥተኛ ሥለሆነ፣

የአማራውን ሠላማዊ ሠልፍ በተመለከተ ድጋፍ ያለው "አብን" ሥለሆነ፣ ይህ ሠልፍ የጎላ የሚዲያ ሽፋን እንዳያገኝና ጥያቄውን ለማድበስበስና አቅጣጫ ለማሳት ታሥቦ እንደሆነ ግልፅ ነው።ይህንንም ያደረጉት ለኢሕአዴግ መጭው ምርጫ ቅድመ ዝግጅት አዴግን ለማጠናከር ካላቸው ሥግብግብነት ነው።

(9)አቢይ!አሜሪካ በነበረበት ጊዜ አማራውን አሥመልክቶ ሲጠየቅ፣የመለሰው አሥገራሚ መልስ"አማራ ላይ የዘር ማጥፋት ተፈፅሟል በመንግሥት ላሉት፣አማራ ክልልም ላነሳ እንደሞከርኩት አማራ የብቻው የዘር ማጥፋት አልተደረገም" አለ።ይህ በአማራ ላይ ያሴረ የትነግን፣የኦነግን፣የጃራን እስላማዊ ኦሮሞና የኦሕዴድን ወንጀል ለመሸፈን"ዓይኔን ግምባር ያድርገው" ዓይነት ሽፍጥና ክህደት እሥከዛሬዋ ዕለት ድረስ እየተፈፀመ ይገኛል።ይህን ክህደት የፈፀመ ሠው እያጀበ ዘጭ ዘጭ የሚለው አማራ ራሱን እንደከዳ ይቁጠረው።

(10)(ሀ) በኦሮሞና በሶማሌ መካከል ተፈጥሮ የነበረውን ቀውስ ለማስቆም መከላከያ ልኮ ከማስቆሙም ባሻገር የተወሰኑትን ከመሪው ከአብዲ ኤሊ ጋር ከማሥወገድም አልፎ እሥር ቤት አሥገብቷቸዋል።

(ለ)ሲዳሞና ወላይታ መካከል የተፈጠረውንም ችግር አሥመልክቶ ባለሥልጣኑ በፈቃዳቸው እንዲለቁ ባሥተላለፈው ቀጭን ትዕዛዝ መሠረት ሥልጣን ለቀቁ።

(ሐ)በወልቃይት፣በአርማጬሆ፣በራያ፣በመተከል፣ ወዘተ፣በአማራው ላይ ግድያና መፈናቀል ሲደርስ፣ትግሬዎች አማራውን ሲጨርሱትም ሆነ የትግሬዋ ኬሪያ ኢብራሂም የምትሰራውንም ወንጀል በዝምታ ማየቱና ማለፉ ድጋፍ እንደመስጠት ይቆጠራል።

(መ) በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መመሪያ ተብዬው፣አገሪቱንና ሕዝቧን የበታተነውን ህገመንግስቱንና የዘርና የቋንቋ ፌደራሊዝምን በአዋሳው ጉባኤ ላይም ይኸው አብዮታዊ ዲሞክራሲያቸው በድጋሜ እንደፀደቀና እንደሚቀጥል ተረድተናል።**ይህም በድጋሜ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሠቆቃ በማር በተለወሰ መርዝ ለማራዘም ነው።**

(ሠ)ዛሬም እንኳን ኦሮሚያ በሚባለው ውስጥ በመዳወላቦ ዩኒቨርሲቲ፣በሀረምያ ዩኒቨርሲቲ፣ በደዴሳ፣በሐረር፣በድሬደዋ፣ ወዘተ በኦነግ እና በግልገል የኦነግ ነፍሰ ገዳይ ቄሮዎች፣የአማራ ሴቶች በቡድን እየተደፈሩ ሲሞቱና ሲታመሙ፣አማራው ሲገደል፣ ሲፈናቀል፣ ንብረቱ ሲቃጠልና ሲጠፋ ዝምታን መረጠ።

(ረ) የኦነግ ግልገል ፋሽስቶቹ ቄሮዎች! በቡራዩ ነዋሪዎች ላይ ግድያና ንብረት ማውደምና ማፈናቀል፣አዲስ አበባም ላይ እንዲሁ ሲፈፅሙ ሳይነኩ፣የአዲስ አበባ ሕዝብ ይህንን ድርጊት ተቃውሞ ሰላማዊ ሠልፍ ሲወጣ ግድያ ድብደባ እንዲሁም እሥራት ተፈፀመበት። በዚህም ሳቢያ የ58 ንፁህን ደም ፈሷል።

ይህንን ተከትሎ (1ኛ) ለማ መገርሳም ወገንተኝነቱ አሥገድዶት "የ6ዓመት ልጅ በአሠቃቂ ሁኔታ መገደልን ተከትሎ እንደመጣ" ከዕውነት በራቀው ንግግሩ፣አፉ ተያይዞበት ራሱን ሲያጋልጥ ታዝበናል።

(2ኛ) በመንግሥት ዜና ማሰራጫም ከቃል አቀባዩ ጀምሮ የኦሮሞ ዘረኛ **ኮሚሽነር በዲ**ንንም ጨምሮ፣ለቄሮዎቹ የወገንተኛነት ሽፋን በመሥጠት፣

ወንጀለኞቹ(ቄሮዎቹ) "ዱርዬዎችና ማንንም የማይወክሉ" የሚል ነጭ ውሸት ሲዋሽ፣የአዲስ አበባን ሠላማዊ ሰልፈኞችም "ቦዘኔዎች ናቸው" ሲል ተደምጧል።

ቀጥሎም እሱ የአነግ ሰው ሥለሆነ "አረንጓዴ፣ቢጫ፣ቀይ"ሠንደቅ ዓላማ ይዘው ለአቢይ ድጋፍ የሰጡት የጎንደር፣የደሴና የአርባምንጭ ሕዝብ፣"ሌባ" ተብለው ተፈረጁ። ይህን በቀውሱ ወቅት የተናገረውን የዘነጋ ካለ፣ ኮሚሽነር በዲ የተናገረውን ተመልሶ ያድምጥ።

(3ኛ)"ቦዘኔዎች"የተባሉት አዲስ አበቤዎች ታፍሰው በማሠልጠኛ ሥም ሲታሰሩ በቴሌቢዥን ታይተዋል። ለዘረኞቹ ቄሮዎች "ዱርዬዎች" የሚል ሽፋን የሰጧቸውና መታሠራቸውን የነገሩን ከኮሚሽነሩ ጀምሮ ሁሉም የኦሮሞ ባለሥልጣናት ናቸው። ግን ታሰሩ ቢባልም፣እንደ አዲስ አበቤዎች በቴሌቪዥን አለመታየታቸው ይታሰሩ አይታሰሩ ህብረተሰቡ እንዲያውቅ ባለመደረጉ፣ዓይን ያወጣ አድሎአዊ አሰራር እንዳለ መነጋገሪያ ሆኗል፣

(4ኛ)5ቱ የኦሮሞ ዘረኛና አክራሪ ድርጅቶች፣የቅድመ አያቶቻቸውን የ16ኛው ክፍለ ዘመን ወራሪዎችን አሥቀያሚ ድርጊት ለመድገም በሚመሥል መልኩ፣የአዲስ አበባን የባለቤትነት ጥያቄ በመግለጫ ሲያነሱና ኦሮሞ ብቻ እንደተጎዳ የዘረኝነት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት የአዲስ አበባን ነዋሪ እንዳሸብሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

(5ኛ)የታወቀው ፀረ አማራና ፀረ ደቡብ የሆነውን ኦሮሞ "ታከለ ኡማን" በአዲስ አበባ ከንቲባነት ሥራ ያሠማራበት ታክቲክ ፣በብዛት ኦሮሞችን አዲስ አበባ ላይ በማሥፈር ቀስ በቀስ ሌሎችን ብሔር ብሔረሰቦች ቤት አልባ በማድረግና በኢኮኖሚ በማዳከም ለመንቀል እንደሆነ የአደባባይ ሚሥጥር ነው።ዳግማዊትንም ከአዲስ አበባ ማንሳቱም ሌላው አጠያያቂ ጉዳይ ነው።

አዲስ አበቤዎችም ባለሥልጣኑ አንድ ዘር ብቻ እየመረጡ ቤት የሚሰጡ ከሆነ ጉም ጉም ማለት ሥለማይጠቅም ሠላማዊ ሰልፍ እያደረጉ ለመብታቸው ይታገሉ።

(6ኛ)እሥካሁንም ድረስ፣ወንጀለኞቹ ቄሮዎች ሳይነኩ፣83ቱ የአዲስ አበባ ወጣቶች "አሸባሪ"ተብለው እንዲታሠሩ ሆነ።

በአጠቃላይ ይህ ሁሉ ቀውስ ከቡራዩና ከአዲስ አበባ ሁኔታ ጭምር ሲካሄድ፣ ዶክተር አቢይ አንድም ጊዜ ድምፁን አለማሰማቱ የፖለቲካ አካሄዱና አቋሙ ጉራማይሌ ከመሆኑም በተጨማሪ ፣በአክራሪ ኦሮሞዎች መልካም ፈቃድ የሚዘወር መሪ በሚመሥል መልኩ ጥርጣሪያችንን ያጠናከረበት ወቅት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ይህ ቁልጭ አድርጎ ያሳየን ባለሥልጣን ነን የሚሉት የት እንደቆሙም ነው። ይህማ ባይሆን ኖሮ "የአቢይ የግልፅነት ዲሥኩር ደብዘው ባልጠፋ ነበር።

ዶክተር አቢይ! ፍቅርን፣ሠላምን፣ዕርቅን፣ኢትዮጵያዊነትንና የኢትዮጵያን አንድነትም ያካተቱ፣የሕዝብን ቀልብ የሳቡ ማራኪና ውብ ቃላትን ተጠቅሞ ፣አንዳንድ ጥገናዊ ለውጦችን እንጅ ሥር ነቀል ለውጥን "በቃል" እንኳን ሲተነፍስ አልተደመጠም።

ዶክተር አቢይ! በአዋሳው የሦሥት ቀናት የኢሕአዴግ ሥብሰባ ላይ፣አብዮታዊ ዲሞክራሲን ከከፋፋዩ ህገመንግሥትና የዘር ፌደራሊዝም ጋር፣ በድጋሜ ከማፅደቅ ይልቅ፣ እንደሚቀየር

በቃል እንኳን ቢናገር ኖሮ፣ ለሥር ነቀል ለውጥ እንደቆመ ፍንጭ ይሆነን ነበር።የሆነው ግን ተቃራኒው ነው።

ይህ የአቢይ የኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ አንድነት ንግግሮች፣ቀደም ብለው የነበሩትን የሕዝብ አመፅ እንቅስቃሴዎች በማዳፈን "በኢትዮጵያ አንድነት መቃብር ላይ፣የተሸነሸኑትን የዘር ክልሎችና የዘር ህገ መንግሥት ተብየዎቹን ሳይሸራረፉ በአንድነት ሥም በሚደረጉ ንግግሮች ብቻ ለማስቀጠል እና በአመፅ የተዳከመውን የኢሕአዴግ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሥርዓት በጥገናዊ ለውጥ ለማጠናከር የታቀደ ከመሆን አያልፍም።ይህን በአሜሪካ ጉዞውም የኢሕአዴግን መጠንከር ከመናገሩም በተጨማሪ በተግባር እየታዬ ነው።

ዛሬ ዶክተር አቢይ የሚለው ከልቡ ቢሆን ኖሮ ፣ "የኢትዮጵያ አንድነት" ዕውን የሚሆነው በ1983ዓም የኢትዮጵያን አንድነት የናደው፣ዛሬ ድረስ በህይወት ያለው **"ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገው "ህገ መንግሥት፣ከ9 የዘርና ቋንቋ ከፋፋይ የክልሎች ፌደራሊዝም " ጭምር ፈርሶ፣በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የተዋቀረ ከዘርና ከቋንቋ የፀዳ ለአሥተዳደር የሚመች በጥልቀት የተጠና ሕዝብን ከሕዝብ የሚያቀራርብና የሚያስማማ፣እኩልነትንም የሚያሟላ ፣እንደ እነአሜሪካም ይሁን እንደ እነሥዊዝ ወዘተ ለምሳሌ "አካባቢያዊ ፌደራሊዝምን ባካተተ ህገ መንግሥት" ሲተካና በወሬ ሳይሆን ከልብ አብሮነታችንን በዚህ ዓይነት "ሥር ነቀል ለውጥ" ተግባራዊነቱን ሥናረጋግጥ ብቻ ነው።**

የኢትዮጵያ ሕዝብም በገዛ አገሩ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንደልቡ ተንቀሳቅሶ በየትኛውም አካባቢ የመሥራትና የመኖር ብሎም የመናገር መብቱ በአጠቃላይ የግለሰብ ነፃነቱ የሚከበረውም ይህ ሲተገበር ነው።

ይህ **ሥር ነቀል ለውጥ** ተግባራዊ ሳይሆን፣**የኢትዮጵያ አንድነት፣ኢትዮጵያዊ አብሮነትና ሠላም ዕውን** እንደማይሆን ለማንም ግልፅ መሆን አለበት።

ይህ ዛሬ ያለው ህዝብን ከህዝብ ሲያጋድል የኖረውና አገር የበተነው፣ ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ ህገ መንግሥት ከዘርና ከቋንቋ ክልሎች ጭምር እሥካልተለወጠ ድረስ፣ ዶክተር አቢይም "አጥፊውን ሥርዓት" ላለመንካትና ላለመለወጥ፣ዙሪያ ዙሪያውን እየሄደና እያሽሞነሞነው፣"ወንጀለኞች" የተባሉትን ብቻ በማባረር ተግባር እሥከቀጠለ ድረስ፣ ትናትናም ሆነ ዛሬ እያመሱን የሚገኙት የይገባኛል ጥያቄዎች ሲያጋድሉን ይኖራሉ።የዘር ግጭትም አይቆምም።አንድ ቦታ እሳቱ ሲበርድ፣ሌላ ቦታ እየተቀጣጠለና ሁኔታው እያገረሸ "የኔ ፣የአንተ" በሚሉ የዘር ክልል አባዜዎች በመወጠር መገዳደሉንና መፈናቀሉን ለማስቆም ዶክተር አቢይ ጥገናዊ እንጅ መሠረታዊ ለውጥ፣ጊዜያዊ እንጅ ዘላቂ መፍትሄ ሊያመጣ አይችልም።

**ቁልፉ ያለው አንድ ቦታ ነው**።እሱም የዘርን ህገ መንግሥትና የዘርን ክልሎች አፍርሶ ከዘርና ከቋንቋ የፀዳ አካባቢያዊ ፌደራሊዝምና ህገ መንግሥት ማፅደቅ ነው።ከዚህ ውጭ የሚደረጉ አካሄዶች የትግሬን የበላይነት በኦሮሞ የበላይነት ከመተካት አያልፍም። መተራመሱ፣መካሰሱ፣መወነጃጀሉ፣መጠፋፋቱ ምንጊዜም አይቆምም።ውሎ አድሮ

እንደ27ዓመቱ አፈናና ጭቆና ከመሆን አይዘልም ምክንያቱም ችግሩ ያለው ሥርዓቱ ላይ ነውና።

ይህ ተግባራዊ እንዳይሆን ትነግና አነግ እንዲሁም ሌሎች አክራሪዎች! ዛሬም ድረስ በአማራ ላይ ግድያ ከመፈፀምም አልፈው በጠቅላላ በአገሪቱ ውስጥ ቀውስ እንደፈጠሩ ነው። ምክንያቱም የሠረቋቸው መሬቶች ወደባለቤቶቹ እንዳይመለሱባቸውና አማራውም እንደተዳከመ እንዲቀጥል ካላቸው አቋም በመነሳት ነው ።

**ማሳሰቢያ!** እስከዛሬ የአማራው በተናጠል መሄድ፣በጠላት አሥጠቅቶታል፣አሥጨርሶታል፣ ተፈናቃይ አድርጎታል።ከእንግዲህ አማራው በአንድነት በመቆም ጠላት የማይበግረው ለህልውናው ዋሥትና የሚሰጥ ኃይል መሆን ይጠበቅበታል። አማራውም በአንድነት እንዲቆም የአማራው ሕዝብ ጫናና ግፊት ማድረግ አለበት።

አንድ የማይሆኑ ከሆነ ሕዝቡ ዕርዳታውንና ድጋፉን ያንሳ! መፍትሄው ይህ ብቻ ነው።

**በመጨረሻ!** ለአማራው የቀረበለት ምርጫ አንድ ነው፡፤በቅድሚያ ለአማራው የሚቆም መንግሥት እንደሌለው በ27ዓመት የተሰራበት የግፍ መጠን አሥተምሮታል።ሥለዚህ መፍትሄው በህጋዊ ተብዬው ከመደራጀት ባሻገር በህቡዕ ተደራጅቶ መታጠቅ ብቻ ነው ። 27ዓመት በባዶ እጃችን የውሻ ሞት ሞተናል።ከእንግዲህ ሲገድሉን ለመግደል ከመታጠቅ ውጭ አማራጭ የለንም።

ዘረኛው ህገ መንግሥት ከተቀየረና የዘርና የቋንቋ ክልሎች ፈርሰው በአካባቢያዊ ክልሎች ከተተኩ፣በዚህ ሳቢያም የተፈናቀሉትም ወደቦታቸው ከተመለሱና እኩልነት ከተረጋገጠ፣ አማራው! ትጥቁን ይፈታል።

ዛሬ ያለው ህገ መንግሥትና የዘር ክልሎች እንዲቀጥሉ ከሆነ ግን አማራው ትጥቁን አጠናክሮ የተወሰዱበትን ርሥቶቹንና ግዛቶቹን ማሥመለስ፣የተፈናቀሉትንም ወደቦታቸው መመለስ አይቀሬ ነው።

ከዚህ ውጭ የሚደረደሩት "በህጋዊ መንገድ ወይም የህግ የበላይነት" የሚባሉት ለአማራው ፍትህ ሳይሆን የአማራው መጥፊያ መሣሪያዎች እንደሆኑ አውቀን መቁረጥ የግድ ነው።

**ታግሎ ህልውናንና ማንነትን ማሥከበር የተፈጥሮ ህግ ነው!**

**እሥከዳር በላቸው**